የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ቁጥር OFAGF-03.9/2/35
ቀን 14/06/2015

ለክብርት ዶ/ር ምስራቅ መኮንን

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት ኃላፊ

ለክቡር ዶ/ር እንዳለ ሀይሌ

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዋና ዕንባ ጠባቂ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል፣</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን ሕዝብ ዕንባ ጠበቂ ተቋምን የ2014 በጀት ዓመት የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 6 ገጽ ኦዲት ሪፖርት እና 3 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች በድምሩ 9 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላከን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጌታሁን ጃምቤ
ፋይናንስና ኮሚሽን መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም
# የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት
# ኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2015

አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

# የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት

# ኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2015

አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# ህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም
# የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት
# ኦዲት ሪፖርት

የካቲት /2015

አዲስ አበባ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም
## የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ
## ኦዲት ሪፖርት

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የተመደበለትን የመደበኛና ካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የመንግስት የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆን በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም  የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30ቀን የ2014 ዓ.ም ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው በአዋጅ በተፈቀደው በጀት በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁና የተከፈለው ወጪና በጀት አጠቃቀሙ የፋናንስ አስተዳደር አዋጅን ደንብንና መመሪያን ጠብቆ የተከናወነ በመሆኑ በእኛ አስተያየት በተቋሙ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች እና የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓቱ አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች(Emphasise Matters)**

**1. ያለአግባብ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ**

ተቋሙ የፈጸማቸው የካቲት 16/2012 የወጣ የመንግስት ሠራተኞች የአገር ዉስጥ የቀን ዉሎ አበል አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 3/2012 ክፍል ሁለት የቀን ዉሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም አንቀፅ 5 የቀን ውሎ አበል ተመንና አከፋፈል በተመለከተ የቀን ውሎ አበል ተመን የሚሰላው ከአንድ ቀን የውሎ አበል ክፍያ ውስጥ ለቁርስ 10%፣ ለምሳ 25%፣ ለእራት 25% እና ለአልጋ 40% በመመደብ የሚታሰብ መሆኑን ይገልፃል፡፡የኢትዮጵያ ህዝብ አንባ ጠባቂ ተቋም እና በስሩ ያሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የውሎ አበል ክፍያዎችን በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

በተለያዩ ጊዜያት ለመሥክ ሥራ ሄደው ወደ አዋሳ በሚመመለሱበት ወቅት የእራትና አልጋ ተቀናሽ ሳይደረግ በብልጫ የተከፈለ የውሎ አበልብር 3361.ተገኝቷል፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፣**

1. **የንብረት አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፣**

   የፌዴራል መንግስት የንብረት አሰተዳደርና መመሪያ ቁጥር 9/2003 በክፍል አራት አንቀጽ-20 የመንግስት ንብረት ስለማስወገድ በንዑስ አንቀጽ-1 ከፊደል ሀ-መ በተገለጸው መልኩ የማይፈለጉ ንብረቶችን በንዑስ አንቀጽ-2 በተጠቀሰው የአወጋገድ ስርዓት መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች ማስወገድ እንደሚችሉ ተገልጾዋል፡፡ እንዲሁም የተቋሙ የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ እና ቁጥጥር በአዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በመመሪያ በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

__በዋናው መ/ቤት__

- አገልግሎት የማይሰጡ እና የሚወገዱ የተለያዩ ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች በቁጥር 49፤ ኤልሲዲ ፕሮጀክተሮች በቁጥር 6 ፣ ፋክሶች በቁጥር 11 ፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች በቁጥር 16 ፣ የተለያዩ ፕሪንተሮች በቁጥር 25፤ የተላያዩ ሞባይል ቀፎ በቁጥር 7 ፣ኢቪዲዮ በቁጥር 2፤ የውሃ ማጣሪያዋሪት በቁጥር 1፣ የተለያዩ ወንበሮች፣አገልግሎት የማይሰጡ በርካታ የመኪና ጎማዎች፤ ቁርጥራጭ ብረቶች፣የተለያዩ መፍቻዎችና መደሻዎች፣ቴሌቭዥን በቁጥር 1፤ ሳይወገዱ በተቋሙ የዕቃ ግምቤት ቤት ውስጥ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ፤

__በኦሮሚያ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት__

- በተቋሙ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ እና ብዛት ያለቸው አገልግሎት የማይሰጡ ሊወገዱ የሚገባቸው የተለያዩ የንብረት ገቢ ደረሰኝ፤ የንብረት ወጪ ደረሰኝ፤ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ፤ የወጪ ቫውቸሮች መገኘቱ፤
- በቁጥር የማይታወቅ የተቀየረ አሮጌ የተሸከርካሪ መለዋወጫዎች፣ብዛት ያላቸው ጋዜጦች፣ዴስክቶፕ ኮምፒውተሮች ፣ወንበሮች፣በእርዳታ የመጡ የዳታ ቤዝ ኬብሎች(ትራክ) በአንድ ላይ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፡፡
- በንብረቶቹ ላይ ቢን ካርዳቸው ኢፍምስ ከመጀመሩ በፊት የነበረ ቢሆንም ኢፍሚስ ከተጀመረ በኃላ በሁሉም እቃዎች ላይ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ

__በሃዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት__

1. ለቋሚም ሆነ ለአላቂ ንብረቶች ገቢና ወጪ እንዲሁም ከወጪ ቀሪ የሚመዘገብበት መዝገብ ያልተቋቋመ መሆኑ፡-
2. በንብረቶች ላይ ቢን ካርድ የማይንጠለጠል መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡-
3. አገልግሎት የማይሰጡ ቋሚና አላቂ፤እቃዎች በአንድ ላይ የሚቀመጡ መሆኑን;

መሆኑ በኦዲት ታውቋል።

1. <u>የተሸከርካሪ አያያዝና አጠባበቅ</u>

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 20 ከተራ ቁጥር 1-2 በተመለከተው መሰረት የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት እንዲሰጥ ተገቢው ጥገናና እንክብካቤ የሚደረግለት መሆኑን እና በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 20 ተራ ቁጥር 1 ከፊደል ሀ-መ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ሊወገዱ የሚገባቸው ንብረቶች መወገዳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-02095 ቲዮታ(ጃፓን)፤4-12201 አውቶሞቢል(መርቸዲስ) እና 4-0200 ሞተር ሣይክል (ያማሃ) ከ5 ዓመት በላይ የቆሙ መሆኑ እና
- አንድ ኒሳን ፓትሮል የሰሌዳ ቁጥር 4-00055 ለረጅም ጊዜ የቆሙ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

<u>ክትትል ኦዲትን በተመለከተ</u>

በተቋሙ ስም ላልተመዘገበ የሞባይል ስልክ የአገልግሎት ክፍያ ብር 3,199.39 በተቋሙ ስም ላልተመዘገበ የሞባይል ስልክ የአገልግሎት ክፍያ የተከፈለው ከሚመለከተው አካል ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

<u>የህግ ጉዳዮች በተመለከተ(Compliance Issue)፤</u>

1. <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና አገልግሎት መ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ ርዕሶች በድምሩ ብር 227,909.96 ከአንድ ከወር እስከ 3 አመት የቆየ በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

2. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ በተመለከተ</u>

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ፣ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተከፋይ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከፊደል ሀ-ሠ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እየተከፈሉና እየተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ተቋሙ በሰኔ 30/2014 ዓ.ም በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ የሚታየው በሂሳብ መደብ 6173117/5028 ብር 12,473.69 ከሰስት ዓመት የቆየ በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ በኦዲት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት